# ኢሳትን የማያውቅ “ሰው” ከዚህ አለ።

ኮስታሮቹ የአበሻ ልጆች አጥበቀን የያዝነው አንድ ልማድ አለን።ለወሬ የቸኮለ ካለ እንዲረጋጋ እምከረዋለሁ። አዲስ ነገር ልንግራችሁ አይደለም።እኔ የማካፍላችሁ ያለ የነበረውን ወደፊትም የሚኖረውን ነው።”አብረን እንብላ” የምንለውን ነገር።ሌላ አዲስ ነገር የለም።እርግጥ ነው አብረን መብላታችን አንዱ መለያችንና ውበታችን ነው።አንዳንዶቹ እንደ ጫጩት ተሰባስበው ይበላሉ እያሉ ሊተቹን ቢሞክሩም እኛ ኮስታሮቹ የአበሻ ልጆች ግን የቀናተኛ ወሬ ብለን ከማለፍ ውጭ የምንለው ሌላ ነገር የለንም።አንድ ቀን ግን ለጓደኛየ ዓለም ይቀናብናል ብየ ሳጫውተው ምን እንዳለኝ ታውቃላችሁ ?”በእኛ የማይቀና የለም አለኝ።የከፍላችን ነጭ ተማሪ እንኳን ሳትቀር በእኛ ሴቶች ትቀናለች” ብሎኝ እርፍ።እኔ ግን ይህን አባባል ሰምቼ እንዳልሰማሁ ሁኜ አልፌያለሁ።ሰምቶ እንዳልሰማ መሆንን ለምደነው የለ እንዴ ? በህይወት ያቆየንስ ይሄ ሳይሆን ይቀራል ?ሰምተን እንዳልሰማን መሆንን ያስተማረን ማን ነበር እርሱ ? ያስተማረን ካለ ማለቴ ነው።

እኛ ግን አደገኛ ዜጎች እየሆንን ነው ልበል ?በቃ ለግላችን ጥቅም ካላገኘን በቀር ለጋራ ጥቅም አብሮ መሥራትን አናውቅም ማለት ነው ?እግር ኳስ የጋራ ጥረት የሚጠይቅ ነው።እኛ ግን በዚህ የተሳካልን አይደለንም።በሌላ በኩል በሩጫ የሚደርስብን አልተገኘም።ለምን ቢሉ የጋራ ጥረት አለመጠየቁ ብቻ ሳይሆን በይበልጥ ጥቅሙ የግል ስለሆነም ነው። ሯጮቹ ለሽልማት ሲሰለፍ ስቅስቅ ብለው የሚያለቅሱት የአገር የባንዲራ የወገን ነገር ሆዳቸው ገብቶ መስሎኝ ነበር።ግን አይደለም። የአንድ ሁል ግዜ እያለቀሰ የሚያስለቅሰን ታላቅ ሯጭ ልጅ እስኪ አንድ ተረት ንገሪኝ ተብላ ስትጠየቅ ምን እንዳለች ሰምታችኋል ? እንዲህ አለች “Daddy what is he saying?”ብላ ወደ አባቷ ጮኸች።አገርን ማክበር የት ጋ ይሆን የሚጀመረው ? ይህች ልጅ ከአሁኑ ኢትዮጵያዊነቷን እንድትንቅ ተደርጋ እያደገች ነው።ይህች ልጅ የሚነገራት በጋራ ሊያበለጽጉን የሚችሉ ደጋግ ተረቶቻችን ሳይሆኑ ሌላ ሌላ ነገር ነው።የታላቁን ሯጭ እንባ በትዝብት አይተነው ወደ ጉዳያችን እንገባለን።ከየት ተነስቼ የት እንደደርስኩ እንጃ ቢሆንም ይሁን።

እናም አበሾች በግላችን የሚጠቅመንን ነገር ለማግኘት የማንወርደው ቁልቁለት የማንወጣው አቀበት የለም። ተስፋም የሚያስቆርጠን ምንም ነገር የለም።በጋራ ለመሥራት ግን ገና ከመጀመራችን ተስፋ ቆርጠን ተኮራርፈን ተካሰን ነገሩን ሁሉ የእንቧይ ካብ አድርገነው እናርፋለን።እንዲህ ዓይነት ዜጋ አደገኛ ይመስለኛል።አደገኛ ቦዘኔ የሚባል ካለም አገር ለሚባል ነገር ምንም የማይጨንቀው መሆን አለበት።

ይህች የምንኖርባትን አገር አሜሪካንን ለማልማት ኢትዮጵያዊያን አባቶቻችን ያበረከቱት አስተዋጽኦ የከፈሉት መስዋእትነት አለመኖሩን ለማሰብ ምንም ፍላጎት የሌለን ብዙ ነን።እኛ መጥተን ሌሎች ደክመው ባቀኑት ላይ ደረታችንን ነፍተን በነጻነት ያለሃሳብ እንኖራለን።እንዲህ ዓይነት አገር እንዴት እንደተሰራና በምን ያህል ድካም እንደተመሠረተ ግን ማወቅም መስማትም አንፈልግም።እንዲህ ዓይነቱ ሰው አደገኛ የማህበረሰብ ቀውስ ከሚያስከትሉ ሰዎች መካከል ይመደባል።ዘወትር የሚገርመኝ ግን የኢትዮጵያው ገዥ እንዲህ ዓይነቶቹን ሰዎች አጋሮቼ ናቸው ማለቱ ነው።ዝምተኛና “ጨዋዎች” እያለ ያሞካሻቸዋል።እንዲህ ዓይነቶቹን ዝምተኛና “ጨዋ” ሰዎችን እያንዳንዳችሁ እንደፈለጋችሁ ልቦናችሁ የፈቀደውን በሏቸው።እኔ ግን ምንም አልልም።ኢሳት ከፈለገ ትዝብት በሚለው ፕሮግራሙ ላይ ያቅርባቸው እንጂ እኔ ምንም አልናገርም።

አሜሪካን በፈለገችሁ ሁኔታ ትሰራ የማይገዳቸው አንዳንድ ደጋግ የቅርብ ወዳጆች አሉኝ።ሁል ግዜ አብረን የበላነውን ሁሉ ሲከፍሉ ምንም ቅር የማይላቸው።እንዴት ደጋጎች መሰሏችሁ።በጣም ደጎች።እኔ ግን የእነዚህ ወዳጆቼን የደግነት ምንጭ ፍለጋ ብወጣ ብወርድ አልከሰት ብሎኛል።ለጓደኞቻቸው ለመጋበዝ የሚሽቀዳደሙትን ያክል አገራቸው እርጥባን ስትለምናቸው ትንሽ እንኳን ልቦናቸው አለመደንገጡን ሳይ ግር ይለኛል።እኔ መቸም አይቼ እንዳላየሁ የመሆን ልማድ ባይኖረኝ ኑሮ ስንት ነገር ተናግሬ ነበር።እድሜ ለአይቶ ማለፍ ልማዳችን።ለምሳሌ ያክል ኢሳትን ያቋቋሙ ወገኖች ትንሽ ትኝሽ የገንዘብ እርዳታ ይፈልጉ ነበር።ስንት ኢትዮጵያዊያን ይሄን ለኢትዮጵያ ህዝብ አማራጭ የመረጃ ምንጭ የሆነውን መገናኛ ብዙሃን ለመርዳት ጥረት አደረጉ ? እኔ ቁጥሩን አላውቅም።ሆኖም ግን አገር ቤት ያለው ህዝብ እውነተኛ

መረጃ ባለማግኘቱ ምክንያት የሚደርስበትን በደል የሚያዳምጥ ሂሊና የሌላቸው በርካታ “ጨዋና ዝምተኛ” ኢትዮጵያዊያንን ስታዘብ ቁሜ እገረማለሁ።አንቱየዋ “ጨዋና ዝምተኛ” ተብለው በዓይጋ ፎረም የሚሞካሹትን ዜጎች ምሳሌ ወረድ ብለው ያገኟቸዋል።ብቻ እንደምንም ብለው እስከ መጨረሻው ይዝለቁ።እንዲያው ደፈረኝ አይበሉኝ እንጂ እርስዎ ኢሳትን ረድተው እንደሆን ብጠይቅዎ ይናደዱብኝ ይሆን ? እኔ እንደምጠረጥረው እርስዎ ያው እንደ እኔ $500 ዶላሯን ሰጥተዋል።ተመስገን ደግ አደረጉ።እንዲህ ነው እንጂ መረዳዳት።በጎ ነገር ሲደረግ አይዞህ ማለት።እንግዲህ አልረዱ እንደሆነ ግን ከዘመኑ “ጨዋና ዝምተኛ” ዜጎች መካከል እንዳያስመድቦት መጠንቀቅ አለብዎት።

ወዳጆቼ ሆይ ኢትዮጵያችን እንዲህ መልኳና ውበቷ ሲጠፋ እያዩ ዝም ማለት የአሪፍ ኢትዮጵያዊ ባህሪይ ነው ብለው ይሆን ዝም የሚሉት ? እኔ እውነቱን ልንገርዎት አሪፍ ኢትዮጵያዊ በዚህ ግዜ ዝም አይልም። አሪፍ ሰዎች ለአገራቸው ኢትዮጵያ ያስቡላታልና እናንተ ዝም ብላችሁ የምትኖሩ ሁሉ አሁን ኢትዮጵያ የት እንዳለች መጠየቅ ብትጀምሩ ምን ይመስላችኋል ብየ ስጠይቃችሁ ስልኬን ማንሳት እንዳትተው።መቸስ እንዲህ ብየ የመከርኳቸው ብዙ የማውቃቸው ሰዎች ስልኬን ማንሳት ከተው ሰንበተዋል።እኔም መንገዱን ጨርቅ ያርግላችሁ ብየ ዝም ብየአለሁ።

አሁንም ውድ የአገሬ ልጆች ሆይ እባካችሁ አገራችሁን አስቡ ብየ እመክራችኋለሁ።ካኮረፋችሁ ግን እኔ የማደርገውን አውቃለሁ።ግን ምን አደርጋለሁ ያው ታዝቤ ዝም ጭጭ እላለሁ እንጂ።ለማንኛውም ሁላችንም በያለንበት ጥቂት ጥቂት ነገርን ማድረግ እንልመድ።ሁላችንም ለነጻነታችን ብለን ጥቂት ጥቂት ማድረግ ብንችል እኮ አገራችን በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ አትገኝም ነበር።ከብት ገለን ጥሬ ሥጋውን ለመብላት እንደምንሰባሰብ ሁሉ ለአገራችን በጎ ነገር ለማድረግ ስንጠራም ብንሰበሰብ ዜጎቿ የማይሰደዱባትና የችጋር ምሳሌ ያልሆነች አገር ትኖረን ነበር። እንግዲህ ለብልህ አይመከሩ ለጎበዝ ... የሚባልላችሁ ዓይነት ስለሆናችህ ከዚህ በላይ ምንም አልልም።የሚያስፈልጋችሁ ምክር ሳይሆን አስታዋሽ ስለሆነ ላስታውሳችሁ ብየ ነው።እናም አገር ከከብት ጥሬ ሥጋ ትበልጣለች እና አገራችሁን አስቧት ስላችሁ እንደማትከፍብኝ ተስፋ አደርጋለሁ።አስታዋሽ አያሳጣህ ብለው ይመርቁኝና ልቀጥል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ አንድ ይህ ጉድይ የሚከነክነው ጓደኛየ እንዲህ የሚል ጥያቄ አንስቷል።”እነዚህ ከአገራቸው በላይ ለጥሬ ሥጋ ክብር የሚሰጡ አበሾችን ሠው ያረገቸው ሚስጥር ምን እንደሆነ በአስቸኳይ ተይዘው የሚመረምራቸው አንድ ጥበበኛ ይፈለግ።” አንፈርድበትም።እውነት አለው።በመስክ ላይ እንደሰፈረ አንበጣ ኮስታሮቹ የአገራችን ልጆች ጥሬ ስጋ ያለበት ሰፍረው ሲያይ ግዜ ከንክኖት እኮ ነው “ለምን በእነዚህ አበሾች እንደተገረምን እንኖራለን ሲል የሚጠይቀው።” እኔ ግን አይ እንዲህ እንኳን አታማርር ከሰው ጋርም ትጋጫለህ ብየ ብመክረው ይባስ ብሎ “ካገሩ በላይ ለጥሬ ሥጋ የሚሰበሰብ ሰው አይባልም ጥንብ አንሳ ነው”ብሎኝ እርፍ።አይገርምም ? እኔ ግን ከመገረም አልፌ እነዚህን “ጨዋና ዝምተኛ” ወገኖቼን ስለነካብኝ ተናገርኩት።በየቦታው ስንት አናጋሪ አለ መሰላችሁ ? እንዲህ ተናግሮ ከሚያናግርዎ ይሰውርዎት።

በየቦታው ስንት የሚያስገርም ነገር አለ መሰላችሁ ?እኔን ያስደነቀኝንና ያስገረመኝን ነገር ለእርስዎ ባላካፍል ምቀኛ የሆንኩ ስለሚመስለኝ እንደሚከተለው አጫውቶታለሁ።ይህ ነገር አልገረመኝም ብለው ዝም ካሉ ግን እኔ ራሴ ተመልሼ ግርምት በግርምት ልሆን ነው ማለት ነው።

በአንድ ተክለሰውነት ውስጥ ሁለት ሰው አየሁና ገረመኝ።ሰው ያልሆነውን ለመምሰል ሲሞክር።

ነገሩ እንዲህ ነው።እኔና አንድ ወዳጄ ካበሻ መንደር ከተኮለኮሉ ሬስቶራንቶች መካከል ካንዱ ውስጥ ምሳችንን ልንበላ ዘለቅን።ምሳም አዘን እየጠበቅን ሳለ አንዱ ወዳጄን በሩቁ የሚያውቀው ኮስታራ አበሻ ገባ።ይህ ሰው አለባበሱ ከማማሩ የተነሳ የመሣፍንት ዝሪያ ያለው ይመስል ነበር።መሳፍንታት ያምሩ የለ እንዴ ?ያው የውበታቸው ምንጭ እኛ ድሆች መሆናችን ከፋ እንጂ እነርሱሥ ደም ግባት አላቸው።የቀደሙት ነገስታትና መሳፍንት በድሃው ወዝም ቢሆን የሚያስመሰግን ደም ግባት ነበራቸው።ያ ሁኖቹ እነመለስ ዜናዊ ግን...እረ ዴያ እነዚህን ከንፅፅር ማስገባት አያስፈልግም። ምንን ከምን እናነጻጽራለን ወዳጆቼ ?እነዚህን ከእነዚያ ጋር ማነጻጸር አይገባም።አይነጻጸሩምና።እነ መለስ ግን ከመሳፍንቶቹ ወይም ደግሞ ከደርጎቹ ጋር ካልተነጻጸርን ሞተን እንገኛለን እያሉ ነው።

ለማንኛውም እነዚህን እነተዋቸውና ወደ ራሳችን እንግዳ ሰው እንመለስ ።

አዲሱ ሰው ጺሙን "O" ቅርጽ ከርክሞታል።በነጭ ሸሚዙ ላይም አንዲት ጥቁር ካራባት አንጠልጥሏል። አመድማ ኮት ጥቁር ሱሪ አድርጓል።ጽድት ያለች ጫማ ተጫምቷል።በሲያትል ከተማ ካራባት አድርጎ የሚንጎራደድ አበሻ ማየት ብርቅ ነው።ይህን ሰው እንዲህ ሽክ ብሎ ሳየው አንዳች ዓይነት ቢሮክራት ሳይሆን አይቀረም ብየ ጠረጠርኩ። አዋቂ የሚያስመስለውን ኮትና ሸሚዝ እንዲሁም ሱሪ በማጥለቁ ከዚያች ኢትዮጵያ ከምትባል አገር በስደት የመጣ ፊደል የቆጠረ ይሆናል ብየ አሰብኩ።በእጁ የያዛትን ቁልፍ መያዣ በጣቱ ላይ እየጠመጠመና እየፈታ ሳየው አንዳች ሃሳብ የሚያኝክ መሰለኝ።እኛም ኢትዮጵያዊያኑ አብረን ለመሥራት ሳይሆን አብረን ለመብላት ታንጾን በኖርነው ባህል መሠረት አብረን እንድንበላ ጋበዝነው። እርሱም በባህላችን መሠረት ከትንሽ መቅደርደር በኋል ተቀላቀለን።

ከዚህ ከማላውቀው ሰው ጋር ወሬ ጀመርን።ጥሎብኝ ዘወትር ወሬየ የሚጀመረው አገር ቤት ምን አዲስ ነገር አለ ብየ ነው።ይህ አለባበሱ አዋቂ ያስመሰለው ግለሰብ "አይ ምን አዲስ ነገር አለ ደግሞ፤ያው ነው ሁሉም ያው ነው ምንም አዲስ ነገር የለም" ሲል መለሰ።

እንዴት አዲስ ነገር የለም ?አዲስ ነገር ሞልቷል እንጂ ለምሳሌ ኢሳት አዲስ ነገር ነው።

"ምንድ ነው ኢሳት ደግሞ ?"አለ አዋቂ የሚመስለው ሰውየ።

ደነገጥኩና አማተብኩ ጓደኛየ ፈገግ አለ።ይህ ሰው ባደባባይ የሚውል ባይሆን ኑሮ ምንም ባልመሰለኝ።ራሱን መስሎ ቢቀርብና እንዲህ ቢለኝ ምንም ባልከፋኝ ነበር።ይህ ሰው እንደ አብዛኞቹ የኢትዮጵያ እናቶች ቢሆን ኑሮ ምንም ባልገረመኝ ነበር።ተገርሜ ሳበቃ ይህን የማላውቀውን ሰው ትኩር ብየ ሳየው ሁለት ስብእና አገኘሁበት።ጉድ እኮ ነው ይህ ሰው ሁለት ነው።አንደኛው ራሱ ሁለተኛው ሌላ ሰውን ለመምሰል የሚሞክረው ሌላ መሆኑን እያጤንኩ ጥቂት ጊዜ ወሰድኩ።

እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ሳለሁ ምግቡ መጣ።ወዳጄ ለጸሎት ጎንበስ አለ እኔም ተከተልኩት።አዲሱ ወዳጃችን ከሁላችን ቀድሞ እጁን ወደ ወጪቱ ሰደደ።እኛ ጸሎታችንን ጨርሰን ቀና አልን።

"እንዴ አንተ አትጸልይም እንዴ ሲል ወዳጄ ጠየቀ"

"አይ ምግብ ቀርቦ ጸሎት ለፈተና ነው" ሲል ተፈላሰፈ።

እኛ እየጸለይን እርሱ እጁን ወደ ወጪቱ አስቀድሞ በመስደዱ እኔ ጸሎቱን ትቼ ስለ አንግዳው ሰው ማሰብ ያዝኩ። ፈተና ማለት ይሄው ነው።

ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ግዜ ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ የሆነ ቴሌብቭን ጣቢያ አግኝታለች።ይህም የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቭዥን ይባላል።ይህ ቴሌቭዥን ከተቋቋመ አሁን ዓመት ሊሞላው ጥቂት ግዜ ብቻ ይቀረዋል ብየ አስረዳሁ። አንድ መብላትና መጠጣት የሚችል ኢትዮጵያዊ ኢሳት መኖሩን አላውቅም ሲል ከመገረም አልፌ ብደነግጥ ለምን ይፈረድብኛል።ልክ ሰይጣኑን እንዳየሁ በስመ አብ ብየ ባማትብስ ለምን የሰው ልጆች ይገረማሉ።አሁንም ኢሳትን የማያውቅ ካገኘሁ ሬሳ በቁም ያየሁ ስለሚመስለኝ አማትባለሁ።በግንባሬ ላይ የመስቀል ቅርጽ ሠርቼ።

አንድ ሁለት ጉርሻ ካጣጣምኩ በኋላ የሚከተለውን ጥያቄ ጠየኩ።

ስማ እንጂ አገር ቤት ስትደውል ምንድ ነው ከዘመዶችህ ጋር የምትጫወተው?

"አይ እኔ ብር ስልክ ብቻ እደውልና እንደደረሳቸው እጠይቃለሁ በቃ ከዚያ ውጭ የማወራው ሌላ ምንም ነገር የለም።እነርሱም ብሩን መቀበላቸውን ብቻ ከመናገር ውጭ ሌላ የሚያወሩት ነገር የለም።ሌላ ነገር የለም።ወሬ ምን ይሰራል። ሥራ ነው የሚያስፈልገው።"ብሎ ሲያበቃ "ብላ ብላ እየበላህ" ሲል ጋበዘኝ።ዓይን ዓይኑን እያየሁ ስላስቸገርኩት።

እንደው ስለሃገር፤ስለጎረቤት፤ስለ ኑሮ ፤ስለ ፖለቲካ ወዘተ ስለመሳሰሉት ነገሮች ማወቅ አትፈልግም ?

"ፖለቲካ ?! ደግሞ ፖለቲካ ምን ያደርጋል?"ከጠየኩት በርካታ ነገሮች መካከል ፖለቲካ የምትለውን መዘ።

ለመሆኑ ላንተ ፖለቲካ ማለት ምን ማለት ይሆን ?

“ፖለቲካና ኮሬንቲ በሩቁ ሲባል አልሰማህም” ብሎ ሲያበቃ ጠቅልሎ ያየዘውን ጉርሻ ወደ አፉ ከተተው።አመጋገቡ ያስደስታል።እንዲህ ሲጎርስ ሴቶች ቢያዩት ሳይወዱት አይቀሩም።

እኔ እርሱን አልሰማሁም እኔ የሰማሁት ግን ፖለቲካ ውስጥ አልገባም የሚል ራሱን በማይረቡ እና በክፉ ሰዎች ለማስገዛት የተዘጋጀ ብቻ ነው የሚለውን ነው።

“አይ እንግዲያውስ አንተ ባገር የለህም ማለት ነው” አለኝ።

እኔ የምልህ ስለ ኢሳት ምን አስተያየት አለህ ?

“እኔ ፖለቲካ ውስጥ የለሁበትም”

ኢሳት እኮ ነጻና ገለልተኛ ሚዲያ ነው።ብዙ ፕሮግራሞችም አሉት።ለምሳሌ የህጻናት፤ስፖርት፤ታሪክ፤ተፈጥሮ ፤ ስፖርት፤ሌላም ሌላም...

“እኔ አያገባኝም።እኔ ከማንም ጋር አልነካካም።”

ኢንቴርኔት ቤትህ አለህ ?

የለኝም።

ምነው ?

“ምን ያረጋል ?እኔ ወሬ አልወድም።”

ኢ-ሜይል ትጠቀማለህ ?

“አልጠቀምም”

እኔ የምልህ የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚንስትር ማን ነበር ስሙ ?

እንጃ አባቱ።

የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ማን ናቸው ?

እንዴ እርሱማ መለስ ዜናዊ ነው።

የአሜሪካን ፕሬዝዳንት ስም ማን ይባላል ?

አይ አንተ ደግሞ።ይህን ማንም ያውቃል።የአሜሪካን ፕሬዝዳንት ስም ኦባማ ነው።

ኦባማ የአባቱ ስም ነው ወይስ የራሱ ስም ?

ስሙ ባራክ ኦባማ ነው።

ታዲያ የእርሱ ስም ማን ነው ?

እንዴ ባራክ ነው ወይስ ኦባማ ? ተወኝ እባክህ የራሱ ጉዳይ ነው።የእርሱን ስም ማወቅ ምን ያመጣልኛል ?

ምንም።ይህ ሰው ጨዋና ዝምተኛ ተብሎ በአይጋ ፎረም የሚሞካሽ ነው።

አንዱ አስገራሚ ሰው ይሄው እዚህ ምግብ ላይ ተገኘ።ከዚያም በል እንካ ይህን ብሮሸር አንብብ ብየ በቦርሳየ ውስጥ ይዥ ከነበረው መካከል አንዱን ሰጠሁት።አገላብጦ ካየ በኋላ “ይሄን ያሳተማችሁበትን ገንዘብ ምን አለበት ለእኔ ብትሰጡኝ” አለ።

መብላቴን ትቼ ተነስቼ ወደ መታጠቢያው ቤት ሄድኩ።

ይህ አበሻ ከብዙ ስንዴዎች መካከል የተገኘ እንክርዳድ መስሎ ታየኝ።አሁን ለዚህ ዓይነቱ እንክርዳድ ምን መልስ ይሰጣል ? ይሄም ኢትዮጵያዊ ነው ብሎ ከማለፍ ውጭ ?

ከዚያ ሻይ ቡና አዘን ቁጭ አልን።አዲሱ ሰውም ስለ አስተናጋጆቹ ቁንጅና ወሬ ጀመረ።

“ይህን ግዜ እኮ ወረቀት የላቸውም።እሽ ብትለኝ እፈረምላት ነበር” ሲል ካዛእንቺስ የኖርኩባትን መንደር ተመኘሁ። የዚህን ሰው አፍንጫ በቡጢ ነስር በነስር ላረገው ፈልጌ።ግን ምን ያደርጋል አሜሪካን ውስጥ ነን።ከዚህ ሁሉ ለምን አንሄድም።ወጣን ።እርሱም ወደ ሚሄድበት ሄደ።ይሂድ አቦ።

✌ ✌ ✌ ✌

መቸስ የኢሳት ነገር ስንት ዓይነት ሰዎችን አስተዋውቆኛል መሰላችሁ ? ብዙ ዓይነት ሰዎችን።ኢሳት መኖሩን ከማያውቁ አንስቶ ኢሳት የወያኔ ነው እስኪሚሉ ድረስ።

ኢሳት የወያኔ ነው የሚሉ ሰዎች ጥቂት የሆነ የአእምሮ ጤንነት የሚጎላቸው ሳይሆኑ አይቀሩም።የሚያዩትን እውነት ሁሉ የሚጠራጠሩ።ወያኔ አንድ የፈጠረልን ነገር ቢኖር ዜጎች ሁሉን እንዲጠራጠሩ ማድረጉ ነው።አንዱ ባንዱ ላይ እምነት እንዳይኖረው አድርጎ ዘረ አበሻ በጥርጣሬ ውስጥ ርስ በራሱ ተፈራርቶ እንዲኖር አድርገውታል።የዚህ ሰለባ የሆኑ ሰዎች ማንንም አያምኑም።ሁሉንም ይጠራጠራሉ።ምንም ጠርጣራ ቢሆኑ ግን ኢሳት የወያኔ ነው ብሎ መጠርጠር የጤና አይደለም።እንዲህ ዓይነቶቹ “paranoid”ሳይሆኑ ስለማይቀሩ የስነ አእምሮ ሃኪም ቢያያቸው መልካም ነው ብየ ዝም ከማለት ውጭ ኢሳት የወያኔ አለመሆኑን ለማስረዳት አልሞከርም። አይደለምና።

ሌሎች ደግሞ አሉ።ኢሳት መፈጠሩን የማያውቁ።እነዚህ ከኮሌጅ ተማሪዎች ጀምሮ እስከ ቤት እመቤቶች ድረስ ያሉትን ያጠቃልላ።የቤት እመቤቶች ላይ አንፈርድም።እነርሱ በቤታቸው መጽሃፍ የለ፤ኢንተርኔት የለ፤ምንም የለም ያለው አንድ ትልቁ “HD” ቴሌቭዥንና ጥሩ ሶፋ ነው።ከተመቻቸው ሶፋ ላይ ሁነው “ኦፕራ ሾውን” እያዩ ግዜያቸውን ያጠፋሉ እንጂ የኢትዮጵያ ጉዳይ አይገዳቸውም ወይም ደግሞ ያገር ጉዳይ አይገባቸውም።በአካባቢያቸው ምን እየተካሄደ እንደሆነም አያውቁም።አገር ማለት ለእነርሱ ዘመዶቻቸው እና ቤታቸው ብቻ ናቸው።እነዚህ ግን አረንጓዴ ቢጫ እና ቀይ ቀለም ሰንደቅ ዓላማችንን በመኪናቸው ላይ አንጠልጥለው ብቅ ለማለት ማንም አይቀድማቸውም።ለንዲህ ዓይነቶቹ ባንዲራ አንድ ደስ የሚል ጨርቅ እንጂ ሌላ አይደለም።ይህ ጨርቅ ተለውጦ ባንዲራ የሚሆነው የአገር ምንነትና ትርጉሙ ለሚገባው ብቻ ነው።ከባንዲራው ጀርባ ያለው ሚስጥርና ለዚያች ባንዲራ የፈሰሰው ደምና የረገፈው አጥንት ለማይገባቸው ሁሉ ባንዲራው ጨርቅ እንጂ ሌላ አይደለም።

እነዚህን ባልቴቶች እንተዋቸውና ወደ ሚያስገርሙን የአበሻ ልጆች እንሂድ።እነርሱም የኮሌጅ ተማሪዎች ይባላሉ። አብዛኞቹ ኮሌጅ ውስጥ የሚማሩ  በአገራቸው ውስጥ ምን እየተፈጸመ እንደሆነ የማወቅ ፍላጎት የሌላቸው ናቸው።ከዚያች ድሃና ምስኪን አገር መጥተው ሲያበቁ ድህነታቸውን ረስተው ልክ የአገሬውን ነዋሪ ለመምሰል ይሞክራሉ።በትውልድ አገር ቋንቋቸው ሰላምታ ሲሰጣቸው በእንግዝሊዘኛ መልስ ለመስጠት ይዳዳቸዋል።አንዳንዶቹ “thick accent” ስላላቸው የሚናገሩት  እንግሊዘኛ ይሁን አማርኛ ለመረዳት እየተቸገርን እናዳምጣቸዋለን።

አንዲት ሁለት ዓስርተ ዓመታት የደፈነች የምትመስል የኮሌጅ ተማሪ አለች።ጸጉሯ እንደ ቴክሳስ ፈረሶች ደህና ተደርጎ ተከርክሟል።በግንባሯ ላይ ድፍት ያለው ጸጉሯ ደግሞ ህንድ አስመስሏታል።አፍንጫዋ ከቅንድቦቿ መካከል ተነስቶ እንደኛ ሰፈር እድር ጡርምባ ጎበጥ ብሎ ወደ ታች ወርዷል።ዓይኖቿ እንደ ቤተክርስትያን ሥዕላት ባለሙያ የሳሏቸው ይመስላሉ።የወገቧን ቅጥነት ያየ ይህች ልጅ ምግብ በልታ ስለማደሯ እንዲጠራጠር ታደርገዋለች። ወጣት ከሚባሉት የምትቆጠርና ቆንጆ የምትባል። ከዚህች ቆንጆ ጋር ወሬ ጀመርኩ።እናም...

እንዴት ነሽ ት/ት ሥራ ኑሮ እንዴት ነው ስል ወጌን ጀመርኩ።

እርሷም "ሁሉም አሪፈ ነው" ስትል መለሰች።

አገር ቤት ምን አዲስ ነገር አለ ?

"ምንም አዲስ ነገር የለም"

ለእንዲህ ዓይኖቶቼ አዲስ ነገር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማሰብ ጀመርኩ።ለማንኛውም ስለ ኢሳት ጠየኳት። ይህች ያገሬ ቆንጆ ልጅ ኢሳትን አታውቀውም።አሁን በዚህ ሰዓት ለእኔ ከዚህች ልጅ ቁንጅና በላይ ኢሳት አለ።እናም ኢሳት አዲስ ነገር እኮ ነው ስል መለስኩ።

አዎን ኢሳት አዲስ ነገር ነው።

"ምንድ ነው ኢሳት ደግሞ ?" ልቤ መምታቷን አቁማ እዚያው ፊቷ ድፍት አለማለቴ እኔው ሁኜ ነው።

የምር ኢሳትን አልሰማሽም ?

"አልሰማሁም"

ኢሳት የሚባል ቴሌቭዥን ጣቢያ ከተጀመረ እኮ ዓመት ሊሆነው ነው።አንቺ እንዴት ነው ያልሰማሽው ?ይሄው በየድህረ ገጹ ላይ እኮ አለ።

"የትኛው ድህረ ገጽ ላይ ?"

ሁሉም አፍቃሬ ኢትዮጵያ በሆኑ ድህረ ገጾች ላይ።

"ምንድ ነው አፍቃሬ ኢትዮጵያ ድህረ ገጽ ማለት ደግሞ ?"

ልቤ እንደ ቡልቻ ልብ 72 ግዜ መምታቷን ትታ አንድ መቶ ልትደፍን ምንም አልቀራት።ቡልቻ ምን ችግር አለበት።በእርሱ ግዜ ኢሳት የለ መለስ ዜናዊ የሚባል ኢሳትን ለማጥፋት የድሃውን ገንዘብ በየቦታው የሚበትን ልበ ደንዳና ገዥ የለ እናም የቡልቻ ልብ ዘና ብላ በደቂቃ 72 ግዜ ትመታ ነበር።አሁን ሁሉ ተበላሽቶ እና ሃሳብ በዝቶብን ልባችን 72 ግዜ ብቻ በመምታት ለሰውነታችን ንጽህ አየርና ምግብ ማድረስ እያቃታት በአንድ ደቂቃ መቶ ግዜ መምታት ግድ ሆኖባታል።እንዲህ ካቅሚ በላይ ፈጠን ፈጠን ብላ ባትመታማ ኑሮ  አንዱ ጋ ድፍት ብለን እንቀር አልነበር እንዴ ?አይ መለስ ዜናዊ አንተ ባትኖር ኑሮ እንዲህ አንሆንም ነበር።ግድ የለም አንተ ስትሄድልን ልባችን ዘና ብላ ሥራዋን ትቀጥላለች። ለልባችን ጤንነት ስንል አንተን መታገል አናቆምም።

አፍቃሬ ኢትዮጵያ ድህረ ገጽ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አታውቂም ማለት ነው ?

"አዎን አላውቅም"

ስንት ዓመትሽ ነው ?

"እንዴ እድሜየ ምን ያረግልሃል ?"

እይ እንደው ለማወቅ ብየ ነው።አውቃለሁ ደባሪ ጥያቄ ነው።ግን ስለ እድሜሽ ስትናገሪ የሚያሳፍርሽ ነገር አለ አንዴ ?

እረ የለም።

ታዲያ ስንት ሆነሽ ?

“25 ዓመቴ ነው።”

እደሜዋን ደብቃ ከሆነ የራሷ ጉዳይ ነው።እኔን ምን ቸገረኝ ኢሳትን እስካስተዋወኳት ድረስ።

በዚህ እድሜዋ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን ምንም ነገር ባለማወቋ ቀፈፈችኝ።ቢሆንም ስለ ኢሳት ማስረዳት አለብኝ።ትግል ውስጥ ነኝ አይደል ?ለመሆኑ እድሜያቸው በዚህ ክልል ያሉ ትውልዶች ለአገራቸው ያላቸው አመለካከት ምን ይመስል ይሆን ? ጥናት የሚያስፈልገው ቁም ነገር ነው።

አፍቃሬ ኢትዮጵያ ድህረ ገጾችን ለማስረዳት በአይጋ ፎረም ጀመርኩ።ለምሳሌ አይጋ ፎረም የሚባል ድህረ ገጽ አለ እርሱ አፍቃሬ ኢህአዴግ ይባላል።ለምን ቢባል አይጋ ፎረም ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን ስለ ህወሃት ብቻ ነው የሚጨነቀው።ኢትዮ ሚዲያ ወይም ደግሞ አባይ ሚዲያ እና ሌሎችም አሉ እነዚህ አፍቃሬ ኢትዮጵያ ይባላሉ። አይጋ ላይ ኢሳትን አታገኚም ሌሎቹ ላይ ግን ታገኚያለሽ።ኢሳትን በድህረ ገጻቸው ላይ የሚያስቀምጡ አፍቃሬ ኢትዮጵያ ይባላሉ። በሌላ በኩል ኢሳትን የማያስተዋውቅ ድህረ ገጽ የኢትዮጵያን ህዝብ ነጻነት የማይፈልግ ወይም ደግሞ የሚዲያ ጠቃሚነት የማይገባው ደንቆሮ ኤዲተር የሚያስተዳድረው ድህረ ገጽ ነው ማለት ነው።

ወሬየ የጣማት አትመስልም።እኔ ግን ሰበካየን አላቆምኩም።ቢገባትም ባይገባትም የራሷ ጉዳይ ነው።እኔ ምን ቸገረኝ እርሷ እንደሆን አንድ ግዜ ድብራኛለች።

“ምንድ ነው ደግሞ አይጋ ፎረም ?”አለች በደበረው ድምጽ።

ወይ መከራ።የኮሌጂ ተማሪ ጥያቄ ገረመኝ።ይህች ሴት ስለ አገሯ የሚጽፍ ድህረ ገጾችን ፈጽማ አታውቅም ማለት ነው።

እኔ የምልሽ እስኪ አንቺ የምታውቂውን የኢትዮጵያዊያን ድህረ ገጾችን ንገሪኝ።

እንዴ “ድሬ ትዩብን” አያለሁ።

ድሬ ትዩብ ማለት ዘፈኖችንና ድራማዎችን በድህረ ገጹ ላይ እየለጠፈ ወጣቶችን ለመያዝ የሚጥር ድህረ ገጽ ነው። ልጅቷም “ከድሬ ትዩብ” ላይ ሙዚቃዎችንም ድራማዎችንም በነጻ እየኮመኮመች ድርማዎቹና ሙዚቃዎቹ እንዴት ባለ ድካም እንደተሰሩ ሳትጠይቅ ደስ ብሏት የምታድረ ነች።

ሌላስ የምታውቂው ድህረ ገጽ አለ?

“ሌላ አላውቅም”

ኢሳትንም አታውቂም።

“ስለ ኢሳት ንገረኝ እስኪ “አለች

ኢሳት ማለት የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቭዝን ማለት ነው።የተቋቋመውም በኢትዮጵያዊያን ሲሆን ከውጭ አገር ሁኖ ወደ ኢትዮጵያ ሃያ አራት ሰዓት ይተላለፋል።ልክ እንደ “MSNBC”ወይም ደግሞ እንደ “አል-ጀዚራ” ማለት ነው።

“ሃያ አራት ሠዓት ይተላለፋል ?”

አዎን ሃያ አራት ሠዓት ይተላለፋል።

“እስኪ ቤት ስሄድ አየዋለሁ።”

ተመስገን ይህች እንኳን ኢንተርኔት ትጠቀማለች።

✌ ✌ ✌ ✌

ደግሞ ሌሎችም አሉ።የዚያች አገር ህዝቦች ነጻነት ማጣት የሚያስጨነቅቻው።እዚህ ጋ አንዱንና ለየት ያለ ሃሳብ የመሰለኝን እገልጻለሁ።መቸስ ሁላችንም በተለያየ መንገድ ከትውልድ አገራችን ተሰደን በየቦታው ፈሰናል።በስደት ወደ ሲያትል ከመጡ ዘለግ ያለ ግዜ የሆናቸው አንድ ደግ ሰው አሉ።የኢሳትን ወሬ ከሰሙ ጀምሮ እንቅልፍ የሚያጡ ናቸው።

እርሳቸው ያሉኝንና ደስ ያሰኘኝን ሃሳብ አብረን እንየው፡

አባቴ እርስዎ አሁን አርጅተዋል።ለምንድ ነው ለኢሳት ከሌልዎት ብር ላይ $500 ዶላር ለመስጠት የወሰኑት ?

“ስማ ልጄ” ሲሉ ጀመሩ “ስማ ልጄ እኔ በዚያች አገር ብዙ ተጠቅሜአለሁ።ለዚያች አገር ውለታየን መመለስ እፈልጋለሁ።አሁን ኢሳት የሚያሳምነኝን ሥራ እየሰራ ስለሆነ ይህን ሚዲያ መርዳት አስፈላጊ እንደሆነ አምናለሁ።ስለዚህ ሰዎችንም አስተባብራለሁ እኔም የምችለውን እረዳለሁ።”

አቦ ይመቾት አባቴ።እርስዎ ነዎት ቆንጆ አበሻ ማለት።

እንደህ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ብዙ ቆንጆ ኢትዮጵያዊያን በሲያትል አሉ።ብራቸውን ሰጥተው እርሱም አላረካ ቢላቸው ለልጆች በውርስ ሊሰጥ የሚገባውን ቋሚ እቃ በሙሉ አውጥተው ለጨረታ የሚያቀርቡ።ከእቃ ይልቅ ንጹህና የሰው ልጆች በሰላም የሚኖሩባት አገር ለልጆቼ ባወርስ ይሻላል ብለው የሚያስቡ።ሌሎችም በርካቶች አሉ።ከትርፋቸው ሳይሆን ዋናቸውን የሚሰጡ።እነዚህ የሚረሱ አይደሉም።ገና ወደ ፊት እንጽፍላቸዋለን።እንዘክራቸዋለን።

ብዙዎቹ በዚያች አገር ስም በርካታ ጥቅሞችን አግኝተው ሲያበቁ የአገራቸው ሁኔታ ትዝ የማይሏቸው እንክርዳዶች በሞሉበት በዚህ ዘመን እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያለውን ሰው ማግኘት ያስደንቃል።ሲያትል እንዲህ ዓይነት ውብ ኢትዮጵያዊያን ያሉባት ከተማም ነች።ሰው ማለት ሰው የጠፋ ግዜ ሰው የሚሆን ማለት ይሄው ነው።

ሌሎች የቀሩ አሉ።ከዚህም ከዚያም ለመሆን የሚፈልጉ።በጾታቸው ወንዶች የሆኑና ገንፎ በማጎንፋት ብዙ ግዜ የሚያጥፍ።ከዚያም እኔ እኮ ቁርሴን ገንፎ በቅቤ ነው የምበላው ብለው በልበ ሙሉነት የሚናገሩ።አይ የሆድ ነገር...ስለ እነርሱ ወደ ፊት ይጻፋል....ሌላ ቀን...ሲመቸን...እስከ ዚያው ገንፎ ለማገንፋት የምታጠፍትን ግዜ አገራችሁ ያለችበትን ሁኔታ ለመከታተል ብታውሉት የአራድ ልጅ የሚያደርገውን አደረጋችሁ ማለት ነው ብየ ሳልመክር እንዳልፍ ልቤ አልፈቀደም። እናም አገሪቷ ሰው በምትፈልግበት በዚህ ግዜ እናንተ ገንፎ እያጎነፋችሁ ግዜያችሁን በከንቱ አታጥፍ።ነገ ያሳፍራችኋል። ለዛሬው በቃን።

እናንተ የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚያሳስባችሁ ሁሉ ግን እግዜር ይባርካችሁ።

ሰውለሰው

ከሲያትል።

freeme97@gmail.com